ከጎቦ ውቃው ጥቅምት 9/2000
ዊኒፔግ- ካናዳ

# “ቦምቡ-ፍቅርሽ-ሲፈነዳ”

“ቦምቡ ፍቅርሽ ሲፈነዳ”
ሃቅ እውነቱ ሲፈነዳ
ሓቅ አነቀው ምድረ ባንዳ
ሆዱ ገዶት ገባ ዕዳ።
        ሃቁም ተነገረ ያበጠው ፈነዳ፤
        ስርየት የግድ ነው. . .
        . . . ቢበቃስ ሽርደዳ።
ምንድር ነው ጫጫታ?፤
ምንድር ነው ኳኳታ?
ሃቁም ተነገረ ቋጠሮው ተፈታ
ምንድር ነው ጉምጉምታ?
ይፈለግ ሃኪሙ
ይነቀል አረሙ
ጊዜ አልፎበታል. . .
አይንን ማስለምለሙ፤
የቃላት ጨዋታ. . .
ባዶ እንካ-ሰላንታ. . .
ብልጥነት፤ ውስለታ።

## ውቸው ጉድ!

        ምንድር ሊሰኝ ኑርዋል ድሮ
        ከዚሕ በላይ ባንዳነት
        ከዬሕ ወዲያ “መወየን”
        በወዳጅ ላይ መጀነን
        ሕዝብን ጥሎ ፈጠን-ፈጠን
        “ባለቤቱን ቢንቁት፤ አጥሩን የነቀነቁት”
        የታሰረዉን ሳያስፈቱት
        የሞተው የደማው ሰማዒት
        የትግሉ ባለቤት አገርቤት
        የምን ማደናገር. . .
        በፍቅረ-ንዋይ ስካር
        “ለሌባ ይመቻል. . .
        . . .ይሄ አይነት ግርግር
        . . .የምን ማደናቆር!
        መሽም ወዲያ ጥንቅር!
        “ነጋም” ወዲያ ጥንቅር!

ታዲያማ! የኛውማ ጲላጦስ
ከአገር ውጭ መደነስ
ባንዲራ ለብሶ መቀደስ
አገሬ! አገር ብሎ. . .
የአዞ-እምባ ማልቀስ
አይቻል ለመኖር
ባንድ ዛር፤ባንድ አኪር
ሁሌ ተኮፍሶ. . .
"እኔ አውቅልሃለሁ!". . .
"እኔ እመራሃለሁ!". . .
. . .የሞኝ-አሞኝ ለቅሶ
. . .መልሶ-መላልሶ።

ጉዲ ! ሰዲ!
"ጋሽ መስፍን!" አከብርሃለሁ!
ሃሳብህን አከብራለሁ
ግና ለምን ጉዱን አወጣኸው?
አልጠረጠርኩም ነበር
እንደምትቆም ከ"ሃይሉ" ጋር

ምን ይጠበስ!
ብኸርታው ተገልጧል
ስሩ ተጠቁሟል
መደናገር ይብቃ!
ማደናገር ይብቃ!
መሸም ጦር ሰበቃ
"ነጋም" ጦር ሰበቃ
` የለዘዘ እቃ!-እቃ!

ግና! ግና!
የነጋ-ፅጌ "ፍልስፍና"
የንቀት ዕብሪት ቡደና
"መዋ-ሸዋ-ቀና"
"መቻቻል" ብሎ ድቁና
"ራስ-ሳይጠና ጉተና"
ወይ ስልጠና! ወይ ስልጠና?!

"ያስቀኛል ገንፎ! ከምሳዬ ተርፎ!"

## ደሞ ነገሩና! ደግሞ አሉና!

ከ”መለስ” ጋር ዕርቅ ይቻላል
ፍጥምጥሙ ተፈጽሟል
ለሰማእታቱ-ደም. . .
እኛ ሃላፊነት ወስደናል!
በፊርማችን አፅድቀናል!
ወያኔ ፍቅር ያቃል!
እርግብ ነው! እርግብ ነው ዋኔ
“ወያኔ”ን ተውት ለኔ!
ወያኔ መሃሪ ነው! ይምራል
ስለ ሞቱት ሰማእት. . .
አታንሱበት! አትሞግቱት!
እንዳይከለክለን አዱን-ገነት
ህልም እንዳይሆን “ከንቲባነት”
“ዲሞክራሲም” በሂደት
“እርነትም” በችሮት፤
ከመለስ ጋር እንላላስ!
ከበረከት-ስሞን ይልቅስ
ግን “በሃይሉ” ላይ እንተኩስ
ኢሕአፓን ነው መደምሰስ!
ይልቁንም “ሃይሉ”ን ታገሉት
“እምባገነን ነው” ጠላት
“በታዬም” ላይ ተነሱበት
“ቀንደኛ” የአገር ጠላት
ምን አላት ሁለት-መቶ ነብስ?
ይልቅ “ሕብረት”ን ነው ማፍረስ!
ፀረ-ወያኔን ማፋለስ፤ማተራመስ!።

ማነህ ባለ ሳምንት?
የምትል የሃይሉ ወዳጅ
እጅ የማትሰጥ ለፈረንጅ
የትግሉ ግለት ሲያይል
በየወንዙ ዳርቻ የማትምል
ጅልነት! ጀሌነት! ቀርቷል
ሚና መለየት ይበጃል
ነውና “አለባብሰው ቢያርሱ፤በአርም ይመለሱ

## ቸር ይግጠመን